**ኖቨምበር 17/2021**

## ስለ ሱፐርኢንተንደንት ፍለጋ ግብረመልስ ዳሰሳ/ቅኝት

የትምህርት ስርዓቱ ተማሪዎችን ለኮሌጅ እና ለስራ ስኬት እያዘጋጀ በመሆኑ "Hazard, Young, Attea and Associates" ከተባለ ድርጅት ጋር በመተባበር ቦርዱ MCPS ን የሚመራ ጠንካራ ሰው ለመቅጠር ቁርጠኝነት አለው። ፍለጋው በዚህ ዓመት ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ባለ ባለድርሻ አካላት በተሰበሰቡት አስተያየቶች ግብአት መሠረት የቦርዱን ዋና ዋና እሴቶች፣ ስልታዊ የቅድሚያ ትኩረቶችን እና አስፈላጊ የመሪነት ባህርይን መሠረት በማድረግ ይመራል። ከቀጣዩ ሱፐሪንተንደንት ስለሚጠበቁት ወሳኝ ባህሪያት ቦርዱ በተለያዩ መንገዶች ከህብረተሰቡ የምክረሃሳብ ግብዓቶችን ይሰበስባል፣ይህም የሚደረገው በዳሰሳ ጥናት፣ በቨርቹወል የታወን ሆልስ ውይይቶች፣ በቃለመጠይቆች እና በማህበረሰብ መሪዎችና ቡድኖች ላይ በስፋት በማተኮር ይሆናል። ይህ ሁሉ የመረጃ አሰባሰብ ሂደት ሲከናወን ስለሚቀጥለው ሱፐርኢንተንደንት ምርጫ ግንዛቤ ይሰጣል።

ስለ ኃላፊነት ቦታው መግለጫ እዚህ ይመልከቱ። የዳሰሳ ጥናቱ እዚህ ይገኛል።

## ረቡዕ፣ ኖቨምበር 24 በታንክስጊቪንግ "Thanksgiving" ዋዜማ ትምህርት ቤቶች እና ጽ/ቤቶች ዝግ ይሆናሉ።

የትምህርት ቦርድ ማክሰኞ፣ ኖቨምበር 9 ባካሄደው ስብሰባ ከምስጋና ቀን "Thanksgiving" በፊት ሁሉም ትምህርት ቤቶች እና ቢሮዎች ረቡዕ ኖቨምበር 24 ለበዓል ዋዜማ ዝግ እንዲሆኑ ውሳኔ ሰጥቷል። በመጀመሪያ ታቅዶ የነበረው ኖቨምበር 24 ሁሉም ሰራተኞች እና ተማሪዎች በቅድሚያ የሚለቀቁበት ቀን እንደሚሆን ነበር። ነገር ግን በአሁኑ ውሳኔ መሠረት ትምህርት ቤቶች እና ቢሮዎች ከረቡዕ፣ ኖቨምበር 24 እስከ አርብ፣ ኖቨምበር 26 ዝግ ይሆናሉ። የልጅ እንክብካቤን በሚመለከት እንደ መጀመሪያው መርሃ ግብር ሊቀጥል ይችላል። እባክዎን ዝርዝር ሁኔታውን ለማወቅ አገልግሎት ሰጪዎቹን ያነጋግሩ። ሰኞ ኖቨምበር 29 ትምህርት ቤቶች እና ቢሮዎች እንደገና ይከፈታሉ።

## ስለ ተማሪዎች ሠላም እና ደህንነት ከጊዜያዊ ሱፐርኢንተንደንት የተላከ መልእክት

ምናልባት ያመለጠዎት ከሆነ፣ ይህ የተማሪዎች ሠላም እና ደህንነትን የሚመለከት መልእክት ማክሰኞ፣ ኖቨምበር 9 ለቤተሰቦች በኢሜል ተልኳል። ኦርጅናል መልእክቱ ከዚህ በታች በድጋሚ ተላልፏል።

ውድ ወላጆች፣ ተማሪዎች እና የማህበረሰብ አባላት
በዛሬው ቀን የምፅፈው በትምህርት ቤታችን ግቢ ውስጥ ስለተፈጠሩት ከባድ ክስተቶች እና የተማሪዎቻችንን እና የሰራተኞቻችንን ደህንነት ለማረጋገጥ እየወሰድን ስላለው እርምጃ ለመግለጽ ነው።
በቅርብ ሳምንታት፣ በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ጥቂቶች የጦር መሳሪያ ይዘው የተገኙትን ጨምሮ በርካታ ከባድ ክስተቶች ነበሩ። **በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ምንም አይነት የጦር መሳሪያ እንደማንታገስ ግልጽ ማድረግ እፈልጋለሁ።** በትምህርት ቤት፣ በትምህርት ቤት ንብረት ላይ ወይም ትምህርት ቤት በሚያካሄዳቸው የተለያዩ ዝግጅቶች ላይ የጦር መሳሪያ ይዞ የተገኘ(ች) ማንኛውንም ሰው ወደ ፖሊስ እናስተላልፋለን። ከ MCPS የስነምግባር ህጎች ጋር በማጣጣም ተማሪዎች ከት/ቤት ከባድ የዲሲፕሊን እርምጃ ይወሰድባቸዋል።

ተማሪዎች በትምህርት ቤት ስኬታማ ለመሆን ደህንነት ሊሰማቸው ይገባል። ተማሪዎቻችንን የደህንነት ስጋት እንዲሰማቸው የሚያደርግ ማንኛውም ባህሪ በ MCPS የተማሪዎች ስነምግባር ህግ መሰረት በፍጥነት እርምጃ ይወሰዳል። ከተማሪ ስለሚጠበቅ ባህሪ እና የዲሲፕሊን እርምጃዎች ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎ ስለ መብቶች እና ሀላፊነቶች/ተጠያቂነት የተማሪ ስነምግባር መመሪያ ይመልከቱ ወይም የትምህርት ቤትዎን አስተዳደር ያነጋግሩ።እባክዎ ከተማሪዎ ስለሚጠበቅ መልካም ስነምግባር እና ውጤቶች በቂ ግንዛቤ እንዳለው/እንዳላት ያረጋግጡ።

**እራሱ(ሷ)ን ወይም ሌሎችን ለመጉዳት እያሰበ(ች) መሳሪያ የያዘ(ች) ሰው እንዳለ እርስዎ ወይም ተማሪዎ ካወቃችሁና በትምህርት ቤት ከሆነ፣ እባክዎ ወዲያውኑ ለትምህርት ቤት አስተዳደር፣ ለአካባቢ ፖሊስ ወይም ለሜሪላንድ የትምህርት ቤቶች ደህንነት ክፍል በ 833-632-7233 (24/7 ክፍት ነው) ይግለጹ።**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የተማሪዎቻችንን እና የሰራተኞቻችንን ደህንነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ደንቦች፣ ፖሊሲዎች፣ እና ልምዶች አሉት፣ እንዲሁም የሰለጠኑ አስተዳዳሪዎች እና የደህንነት ሠራተኞች ሁኔታዎችን ለማርገብ/ለመቆጣጠር ዝግጁ ናቸው። ለድንገተኛ አደጋዎች ምላሽ ለመስጠት ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፖሊስ ዲፓርትመንት እና ከሌሎች የአካባቢ ህግ አስከባሪ ኤጀንሲዎች ጋር የተደረጉ ስምምነቶችን በሠነድ ይዘናል። ካውንስለሮች እና ሌሎች የአእምሮ ጤና ባለሙያዎች ማንኛውንም ሁኔታ ተከትሎ የሚሻክሩ ግንኙነቶችን ለመጠገን እና ለማደስ ዝግጁ ናቸው። ማስተማር እና መማር ዋናው ጉዳያችን ቢሆንም፣ ደህንነት እጅግ ቅድሚያ የምንሰጠው ተግባራችን ነው።
ባለፉት ሳምንታት ያየናቸው ከባድ ክስተቶች መንስኤው ምን እንደሆነ ለመናገር አስቸጋሪ ቢሆንም አንዳንድ ተማሪዎቻችን ማህበራዊ እና ስሜታዊ ትግል እንዳለባቸው እናውቃለን። በወረርሽኙ ምክንያት ስለ ማህበራዊ ኢፍትሃዊነት ስጋት እና ሌሎች ምክንያቶች፣ብዙ ተማሪዎቻችን እና ቤተሰቦቻቸው በሚያጋጥሟቸው ግለሰባዊ ጉልህ ተግዳሮች ለሁሉም ሰው በጣም አስቸጋሪ ጊዜ ሆኖ ቆይቷል። ስለ ተማሪ ደህንነት በ**አእምሮ ጤንነት የግንዛቤ ሳምንት** ዋናው ትኩረት ይሆናል። በዚህ ሳምንት ስለሚከናወኑ ተግባራት እና ስለሚጋሩት ሪሶርሶች በቂ መረጃ ለማግኘት እባክዎ ስለ አእምሮ ጤንነት ግንዛቤ ማስጨበጫ ሳምንት የ MCPS ድረ-ገጽ ይጎብኙ። **እርስዎ የሚያውቁ(ቋ)ት እየታገለ(ች) ያለ(ች) ተማሪ ካለ(ች)፣ እባክዎን በትምህርት ቤት የሆነ ሰው እንዲያነጋግር/እንድታነጋግር ያድርጉ ወይም ለሞንትጎመሪ ካውንቲ አስቸኳይ የስልክ መስመር 301-738-2255 ይደውሉ።**

የተማሪዎቻችንን ደህንነት እና ጤንነት መጠበቅ በትምህርት ቤቶቻችን፣ በቤተሰቦች እና በማህበረሰባችን መካከል በትብብር የሚደረግ ጥረት ነው። አብረን በመስራት ተማሪዎቻችን ደህንነት እንዲሰማቸው፣ዋጋ ያላቸው እና ለመማር እና ለማደግ ዝግጁ መሆናቸውን ማረጋገጥ እንችላለን።

ከአክብሮት ጋር
Dr. Monifa B. McKnight Interim Superintendent, Montgomery County Public Schools
ሞኒፋ ቢ. ማክነይት ዶ/ር ተጠባባቂ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት

**አስተማሪዎችን፣ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን እና ርእሰመምህራንን ለሽልማት በእጩነት ጥቆማ ለማቅረብ ክፍት ነው።**

የሚያደንቋቸውን አስተማሪዎች፣ የድጋፍ አገልግሎት ሰራተኞች እና አስተዳዳሪዎችን ለሽልማት በእጩነት ለመጠቆም ጊዜው አሁን ነው። የመጨረሻው ቀነገደብ በቅርቡ የሚጠናቀቅ ስለሆነ ከዚህ በታች ያሉትን ሽልማቶች ይመልከቱ እና ለእርስዎ የበለጠ ትርጉም ያላቸውን የስራ ባልደረቦች ይጠቁሙ። ሽልማቶቹ—
**የሞንትጎመሪ ካውንቲ የአመቱ ምርጥ መምህር(ት) ሽልማት**:- የሞንትጎመሪ ካውንቲ የአመቱ ምርጥ መምህር ሽልማት ከሙአለህፃናት እስከ 12ኛ ክፍል የሙሉ ጊዜ አስተማሪን እውቅና የሚሰጥ ሲሆን ይኼውም ለሁሉም ተማሪዎች ከፍተኛ የአካዳሚክ እመርታ ያሳየ(ች) እና ከሁሉም የአስተዳደግ እና የችሎታ ደረጃ ያላቸውን ተማሪዎች ያሳተፈ(ች)፣ ለአዎንታዊና ምቹ የትምህርት ባህል አስተዋፅዖ ማድረግ እና ከትምህርት ቤት ማህበረሰብ ጋር መልካም ግንኙነት የገነባ(ች) መሆን አለበ(ባ)ት። ተጠቋሚዎች በ MCPS መምህርነት ቢያንስ የስድስት አመት ልምድ ሊኖራቸው ይገባል። የሞንትጎመሪ ካውንቲ የአመቱ ምርጥ መምህር(ት) MCPS ን በመወከል ለሜሪላንድ ስቴት የአመቱ ምርጥ መምህር ሽልማት በእጩነት ይቀርባል/ትቀርባለች። **የመጨረሻ ቀነገደብ፡- ዓርብ፣ ዲሴምበር 17 እስከ እኩለ ሌሊት ይሆናል።**

**የዋሽንግተን ፖስት የአመቱ ምርጥ አስተማሪ ሽልማት፡** ይህ ሽልማት ከቅድመ መዋዕለ ህጻናት እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ የተማሪዎችን የመማር እና የስኬት ፍላጎት የሚያሳድር የሙሉ ጊዜ መምህርን እውቅና ይሰጣል። እያንዳንዱ/ዷ ተጠቋሚ ቢያንስ የአምስት አመት የማስተማር ልምድ እንዲኖረው/እንዲኖራት ያስፈልጋል፣ ከነዚህም ሶስቱ MCPS ውስጥ መሆን አለባቸው። መምህሩ/ሯ ከዚህ በተጨማሪ የተማሪዎችን ግላዊ ፍላጎቶች በመገንዘብ፣ ችሎታቸውን ማበረታታት እና የግል ተነሳሽነታቸውን ማክበርና መንከባከብ ይገባዋ(ታ)ል። እሱ ወይም እሷ ስለ ትምህርቱ ጥልቅ እውቀት እንዲያ(ድታ)ሳይ እና ለተማሪዎች በአመርቂ ሁኔታ የማስተማር ችሎታ ሊኖረው/ሊኖራት ይገባል። ተጠቋሚው(ዋ) ከስራ ጓዶቹ(ቿ) እና ከህብረተሰቡ ጋር የትብብር ግንኙነት ያለው/ያላት እናም የላቀ የአመራር ችሎታ የሚያሳይ/የምታሳይ መሆን አለባት። **ጥቆማ ለማቅረብ የመጨረሻ ቀነገደብ ዓርብ፣ ዲሴምበር 17 እስከ እኩለ ሌሊት ይሆንኒ።**

**ዋሽንግተን ፖስት የአመቱ ርእሰመምህር ሽልማት፡** ይህ ሽልማት ልዩና አመቺ የትምህርት አውድ ለመፍጠር እለት ተዕለት መወጣት ካለበ(ባ)ት ወይም ከሚጠበቅበ(ባ)ት የሥራ ኃላፊነት በላይ ትርጉም ያለው ተግባር ላከናወኑ ርእሰ መምህራን እውቅና ይሰጣል። እነዚህን ሽልማቶች ሲያበረክት የዋሽንግተን ፖስት (The Washington Post) **Company Educational Foundation፤ በት/ቤት የአመራርና አስተዳደራዊ ብቃትና ጥበብን ለማበረታታት እና በዋሽንግተን ሜትሮፖሊታን አካባቢ ለትምህርት መሻሻል ትርጉም ያለው አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት ተስፋ በማድረግ ነው።** ጥቆማዎች በመምህራን፣ በተማሪዎች፣ በቀድሞ ተማሪዎች፣ በወላጆች፣

በአስተዳዳሪዎች፣ ወይም በሰፊው ማህበረሰብ ሊቀርቡ ይችላሉ። **ጥቆማ ለማቅረብ የመጨረሻ ቀነገደብ ዓርብ፣ ዲሴምበር 17 እስከ እኩለ ሌሊት ይሆናል።**

**[በላቀ የትምህርት አስተዳደር እና ሱፐርቪዥን የ ዶ/ር የኤድዋርድ ሸርሊ ሽልማት "Dr. Edward Shirley Award" :]** በየአመቱ የላቀ አስተዋጽኦ ላበረከተ(ች) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አስተዳዳሪ ወይም ሱፐርቫይዘር እውቅና ለመስጠት፣ ብቁነት ያላቸው እጩ ርእሰ መምህራንን፣ ረዳት ርእሰ መምህራንን፣ የትምህርት ቤት የቢዝነስ ኃላፊዎች፣ ዳይሬክተሮች፣ ሱፐርቫይዘሮች እና በ MCAAP/MCBOA ዩኒት ሌሎች የአስተዳዳር እና የቁጥጥር ሃላፊነቶችን ያካትታል። የእጩዎች ጥቆማ ከ MCPS ሰራተኞች፣ የስራ ባልደረቦች፣ ጓደኞች፣ ወላጆች እና የማህበረሰብ አባላት ሊቀርብ ይችላል። እራስን መጠቆም/በእጩነት ማቅረብም ቀባይነት ይኖረዋል። **የጊዜ ገደቡ: ሰኞ፣ ጃኑወሪ 10, 2022 እስከ 4 p.m. ነው።**

**[የ ሼርሊ ጄ ሎውሪ ስለ ማስተማርዎ እናመሰግናለን ሽልማት/"Shirley J. Lowrie Thank You for Teaching Award:-]** ይህ ሽልማት ለማስተማር ሙያ ወደር የሌለው ትኩረት በመስጠት አስተዋጾ ላደረጉ የኤለመንተሪ ት/ቤት መምህራን እውቅና ይሰጣል። እነዚህ የኤሌመንታሪ ት/ቤት መምህራን፣ ከቅድመ-ሙዋእለ ህፃናት እስከ 5ኛ ክፍል፣ በየእለቱ ከተማሪዎች ጋር በመማርያ ክፍል የሚሰሩ፣ በትምህርቱ ሰፊ እውቀት እንዳላቸው በተግባር ያሳዩ፣ እና የትምህርቱን ፍሬነገር በሚያመረቃ ሁኔታ ለተማሪዎች ማስተላለፍ የቻሉ መሆን አለባቸው።ተጠቋሚው/ዋ፣ተማሪዎች ስኬታማ ለመሆን የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ፣ ተጨማሪ ጥረት የሚያ(ምታ)ደርግ መምህር መሆን አለበ(ባ)ት። **የመጨረሻው ቀነገደብ፡ ዓርብ፣ ዲሴምበር 17 እኩለ ሌሊት**

**[አመታዊ የማርክ ማን ሱፐርኢንቴንደንት የላቀ ብቃት እና መስተጋብር ሽልማት:]** በ1991 የተመሰረተው ይህ ሽልማት የ MCPS ርእሰ መምህራንን የአካዳሚክ ልህቀትን በማበልፀግ፣ አወንታዊ ግንኙነቶችን እና የማህበረሰብ ተደራሽነትን በማዳበር ላይ እውቅና ይሰጣል። እንደዚህ ዓይነት ጥረቶችና ችሎታዎች በ 1988 ከዚህ ዓለም በሞት በተለየው ማርክ ማን (Mark Mann)፣ የፓርክላንድ ጁኒየር ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Parkland Junior High School) ርእሰመምህር በአርአያነት ጎልተው ይታዩ ነበር። ባለፉት አመታት የተደረጉ ጥቆማዎች መደገም ይችላሉ። **የመጨረሻው ቀነገደብ፡ ዓርብ፣ ዲሴምበር 17 እኩለ ሌሊት ይሆናል።**

**[የአመቱ ምርጥ የድጋፍ አገልግሎት ሰራተኛ:]** ይህ ሽልማት ለ MCPS የላቀ አስተዋፅዖ ያበረከተ(ች) የድጋፍ አገልግሎት ሰራተኛን እውቅና ይሰጣል። ተጠቋሚዎች ራሳቸውን ከመሠረታዊ ግዴታዎች ባለፈ የተማሪዎችን ትምህርት ለማሳደግ፣ አወንታዊ ግንኙነቶችን በማዳበር እና ትምህርት ቤትን ወይም ጽ/ቤትን የተሻለ ቦታ በማድረግ ለተማሪዎች እና ለትምህርት ቤት ማህበረሰብ የበኩላቸውን አስተዋፅዖ ያበረከቱ መሆን አለባቸው።

ተጠቋሚዎች ቋሚ የድጋፍ ስራ ባለሙያዎች መሆን አለባቸው፥ በ MCPS ቢያንስ የሶስት አመት አገልግሎት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል። አስተዳዳሪዎች፣ አስተማሪዎች፣ ሌሎች የድጋፍ ሥራ ባለሙያዎች፣ተማሪዎች እና የማህበረሰብ አባላት ሊጠቆሙ ይችላሉ። **የመጨረሻ ቀነገደብ፡ እሮብ ዲሴምበር 22 እስከ 4 p.m.**

**ተጠቅሞ ያበቃለትን ነገር አሻሽሎ እንደገና ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ/"America Recycles Day" የአሜሪካ ሪሳይክል ቀን ኖቬምበር 15 ይከበራል።**

የ MCPS ተማሪዎች እና ሰራተኞች በሙሉ የአሜሪካ ሪሳይክል ቀንን ሰኞ፣ ኖቨምበር 15 ለማክበር በፎል ዘላቂነት አውደ ርዕይ እንዲሳተፉ ተጋብዘዋል። አውደ ርዕይ (ሲምፖዚየሞቹ) የሚካሄደው ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከ 3-3:30 p.m. እና ለአንደኛ ደረጃ (ኤለመንተሪ) ትምህርት ቤቶች ከ 3:30-4 p.m. ይሆናል።

ስለ ትምህርት ቤቶች ዲስትሪክት ስርዓት-አቀፋዊ መልሶ ጥቅም ላይ የማዋል እና አዲስ በጥቅም ላይ ስለሚውሉ ፕሮግራሞች እድገት ይገንዘቡ እና ወረቀትዎ እና ካርቶንዎ ከትምህርት ቤት ከተወገዱ በኋላ ወዴት እንደሚወሰዱ ይስሙ/ያዳምጡ። የጥያቄ እና መልስ ጊዜም ይኖራል።

ወደ ምናባዊ ስብሰባው የሚወስድ አገናኝ/ሊንክ ለመቀበል [እዚህ] ይመዝገቡ። አገናኝ/ሊንክ እስከ አርብ ኖቨምበር 12 ይላካል።

[አሜሪካ የሪሳይክል ቀን]

**ትኩረት ለአረጋውያን! ለሜሪላንድ ፔጅ ፕሮግራም የማመልከቻ ቀን ኖቨምበር 22 ይሆናል**

የ 2021 የሜሪላንድ ጠቅላላ ጉባኤ ፔጅ ፕሮግራም ለ 2021 የሜሪላንድ ጠቅላላ ጉባኤ ለሚካሄድበት ጊዜ ከተመረጡ ተማሪዎች የቨርቹወል እና በአካል አማራጮች ማመልከቻዎችን ይቀበላል። ስለ መንግስት፣ ታሪክ እና አመራር ፍላጎት ያላችሁ ተማሪዎች ይህ እድል ለእናንተ ነው!

ይህ የሚከናወነው በጃኑዋሪ 12 እና ኤፕሪል 11፣ 2022 መካከል ለሁለት ተከታታይ ያልሆነ ሳምንት ይሆናል። በአስራ ሦስተኛው ሳምንታት ክፍለ ጊዜ (ከጃኑወሪ እስከ ኤፕሪል) እያንዳንዱ ፔጅ በክፍለ ጊዜው የመጀመሪያ ኢጋማሽ አንድ ሳምንት ያገለግላል እና በሁለተኛው ኢጋማሽ ክፍለግዜ ለሁለተኛው ሳምንት አገልግሎት ይመለሳል።

የተማሪ ፔጅ የኦንላይን እንቅስቃሴዎች ከሴናተሮች እና ተወካዮች ጋር በኦንላይን በሚደረጉ ንግግሮች እና በኦንላይን የህግ አውጭ ክፍለ ጊዜያት በኮሚቴ ችሎቶች ተሳትፎ ላይ ያተኩራሉ። በአካል ለመሣተፍ የሚቀርበው አማራጭ እያንዳንዱ ፔጅ አናፖሊስ የህግ አውጪ ካምፓስ በአካል ለአንድ ቀን ጉብኝት እንዲመዘገብ ያስችላል።የቀን ጉብኝት ፔጆች ምርጫ የስቴት ሀውስ ግቢን እንዲጎበኙ እና ቼምበር ውስጥ በአካል ተገኝተው ማገልገል እንዲለማመዱ ያስችላቸዋል።

ተጨማሪ መረጃ እና እንዴት ማመልከት እንደሚቻል [እዚህ](#) ማግኘት ይቻላሉ! ማመልከቻዎች **ሰኞ፣ ኖቬምበር 22 እስከ 5 p.m. ድረስ መጠናቀቅ አለባቸው።**

**እለቱን ያስታውሱ! ብሔራዊ የሂስፓኒክ ኮሌጅ ትርኢት ቀን ኖቬምበር 30 ይደረጋል። (National Hispanic College Fair Set for Nov. 7)**

Career Council, Inc. ማክሰኞ፣ ኖቬምበር 30 ከ 9 a.m.–1 p.m. ለተማሪዎች እና ለቤተሰቦቻቸው ነጻ ቨርቹወል የኮሌጅ ትርኢት እያዘጋጀ ነው። ተማሪዎች እና ቤተሰቦች ለዝግጅቱ ለመመዝገብ የት/ቤት ፕሮፋይል ለማግኘት ከትምህርት ቤቶቻቸው የኮሌጅ እና የስራ መረጃ አስተባባሪዎች እና የትምህርት ቤት ካውንስለሮችን ማነጋገር ይችላሉ።

በአውደ ርዕዩ ላይ ለመሳተፍ ተማሪዎች እና ቤተሰቦች [በዚህ ሊንክ](#) አስቀድመው መመዝገብ ይችላሉ።

**ልዩ ፍላጎት ለሚኖራቸው ተማሪዎች ወላጆች/አሳዳጊዎች፡ ቀጣዩ የ SEAC ስብሰባ ኖቬምበር 18 ይሆናል**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የልዩ ትምህርት አማካሪ ኮሚቴ (SEAC) የሚቀጥለውን ቨርቹወል ወርሃዊ ስብሰባ ሐሙስ፣ ኖቬምበር 18 ከ 7 p.m. - 9 p.m. ያካሂዳል። ወላጆች ከሌሎች ልዩ ሁኔታ/ፍላጎት ካላቸው ተማሪዎች ወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር የመገናኘት፣ ከልዩ ትምህርት አስተዳዳሪዎች ጋር ውይይት ለማድረግ እና በዩ ሁኔታ ፍላጎት ርዕሶች ላይ የበለጠ ለማወቅ እድሉ ይኖራቸዋል።

ለበለጠ መረጃ እና አገናኝ ሊንኩን እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ለማወቅ የ SEAC [ድረ ገጽ](#) ይመልከቱ።

ወደ ሊስትሰርቨር (listserve) መካተት ከፈለጉ የኢሜይል አድራሻዎን ለ Rosa M. Aleman በዚህ ኢሜል [Rosa Aleman@mcpsmd.org](mailto:Rosa_Aleman@mcpsmd.org) ይላኩ።

**ቀኑን ያስታውሱ፡- ያገለገሉ መኪናዎች እና ኮምፒውተሮች ዓመታዊ ሽያጭ በመጪው ዲሴምበር 11 ይካሄዳል።**

ስለመጪው የመኪናዎች እና የኮምፒውተሮች ሽያጭ የቀን መቁጠሪያዎ ላይ ምልክት ያድርጉ!

በሞንትጎመሪ ካውንቲ የተማሪዎች አውቶሞቲቭ ትሬድስ ፋውንዴሽን (ATF) እና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፋውንዴሽን (ITF) ጠግነው ለአገልግሎት ያዘጋጇቸውን ያገለገሉ መኪናዎች እና ኮምፒውተሮችን ቅዳሜ ዲሴምበር 11፣ በጌትስበርግ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Gaithersburg High School) ከ 9–11 a.m. ይሸጣሉ። የጌትስበርግ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አድራሻ፡- Gaithersburg High School is located at 101 Education Blvd in Gaithersburg.

መኪናዎቹ እና ኮምፒዩተሮቹ የክፍል ውስጥ እና የላቦራቶሪ ጥናታቸዉ አካል በመሆን በተማሪዎች የታደሱ እና የተስተካከሉ ናቸው። ሽያጮቹ ለተማሪዎች ስለሽያጭ/sales skills/ ችሎታና ልምድ እንዲቀስሙ እድል ይሰጣቸዋል፣ የተማሪ አገልግሎት ትምህርት ሠዓት ያስገኝላቸዋል፣ ስለ ማህበረሰብ ተሳትፎ ጠለቅ ያለ አድናቆት እንዲኖራቸው እድል ይሰጣቸዋል።

ATF አሁንም የመኪና ልገሳ ይፈልጋል፣ ይህም ከ 400 በላይ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች እንዴት ያገለገሉ መኪናዎችን ብልሽታቸውን መፈተሽ፣ መጠገን እና ማደስ እንደሚችሉ እንዲማሩ ይረዳቸዋል። ATF ዓመቱን ሙሉ ከሰኞ እስከ ዓርብ ከ 8 a.m.–3 p.m. ቀጥሎ በተጠቀሱት ቦታዎች ስጦታዎችን ይቀበላል። ደማስከስ፣ ጌትስበርግና ሴኔካ ቫሊ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች፣ በቶማስ ኤድሰን ሁለተኛ ደረጃ የቴክኖሎጂ ት/ቤት እና በሼዲግሮቭ የአውቶቡስ መናኸርያ (Damascus, Gaithersburg and Seneca Valley high schools, at Thomas Edison High School of Technology and at the Shady Grove Bus Depot.) ስጦታዎቹ ታክስ የሚያስቀንሱ ይሆናሉ።

ስለ አውቶሞቲቭ ፕሮግራም ጥያቄዎች ካሉዎት፡- Kelly Johnson በ 240-740-2051 ያነጋግሩ። ለመኪና ልገሳ ቀጠሮ ለማስያዝ፣ Michael Snyder በ 240-740-2050 ያነጋግሩ።

[የኣውቶሞቢሎች ንግድ ስራ ፋውንዴሽን (Automotive Trades Foundation)]

[የመረጃ ቴክኖሎጂ ፋውንዴሽን (Information Technology Foundation)]

**MCPS የቅድመ መዋለ ህፃናት ኮት ድራይቭ ያካሄዳል።**

የ MCPS ቅድመ መዋእለ ህጻናት እና ሄድ ስታርት ፕሮግራሞች ለተቸገሩ ተማሪዎች አዲስ ኮት ልገሳ ይፈልጋሉ። ከ 4-10 ቁጥር ልክ የሚሆኑ የወንዶች እና የሴቶች ጃኬቶችን ወደ Rocking Horse Road Center, 4910 Macon Road, Room 141, Rockville, MD, 20852. ማምጣት ይቻላል። ጓንት፣ ኮፍያ እና ስካርቭም እንቀበላለን።

የሚለግሱትን ከሰኞ እስከ አርብ 9 a.m.– 3 p.m., ድረስ በአካል ተገኝተው መስጠት ወይም ኦንላይን በማዘዝ በቀጥታ ወደ "Rocking Horse Road Center" እንዲደርሱ ማድረግ ይችላሉ። የበለጠ መረጃ ለማግኘት Lisa_W_Conlon@mcpsmd.org ኢሜይል ያድርጉ ወይም 240-740-4530 ይደውሉ።

**መታወስ ያለባቸዉ ቀኖች**

ሐሙስ፣ ኖቨምበር 17 – [የወላጅ አካዳሚ፡ ከታዳጊ ወጣቶች ጋር ስለመግባባት]

ሐሙስ፣ ኖቨምበር 18 - ስለ ፋሲሊቲዎች እና ማካለል የትምህርት ቦርድ ውሳኔዎች

ሰኞ፣ ኖቨምበር 22 - ስለ K-12 (ሁሉም ትምህርት ቤቶች) ቀደም ብለው የሚለቀቁበት ቀን

ማክሰኞ፣ ኖቨምበር 23 - ስለ K-12 (ሁሉም ትምህርት ቤቶች) ቀደም ብለው የሚለቀቁበት ቀን

እሮብ፣ ኖቨምበር 24 - ዓርብ፣ ኖቨምበር 26 - የምስጋና በዓል "Thanksgiving" ትምህርት ቤቶች እና ቢሮዎች ዝግ ይሆናሉ።